የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፫
አዲስ አበባ – ሰኔ ፭ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 43
ADDIS ABABA - 12th June, 1998

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፭/፲፱፻፺ ዓ.ም.
ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..................... ገጽ ፯፻፶፭

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 35/1998
Investment Areas Reserved for Domestic
Investors Council of Ministers
Regulations .......................................... Page 755

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፭/፲፱፻፺

### ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፹፰ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፮(፪) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· አጭር ርዕስ
ይህ ደንብ "ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ስለተከለሉ የሥራ መስኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፴፭/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ
በዚህ ደንብ ውስጥ "የአገር ውስጥ ባለሀብት" ማለት በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፹፰ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፪(፭) የተመለከተው ትርጓሜ ይኖረዋል ።

፫· ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች
ከዚህ ደንብ ጋር ተያይዞ በሚገኘው ሠንጠረዥ የተመለከቱት የሥራ መስኮች በአገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ የሚካሄዱ ይሆናሉ ።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO. 35/1998
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS ON INVESTMENT AREAS RESERVED FOR DOMESTIC INVESTERS

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 6(2) of the Investment Proclamation No. 37/1996 (as amended).

1. *Short Title*
These Regulations may be cited as the "Investment Areas Reserved for Domestic Investors Council of Ministers Regulations No. 35/1998."

2. *Definition*
In these Regulations "Domestic Investor" shall have the meaning assigned to it by Article 2(5) of the Investment Proclamation No. 37/1996 (as amended).

3. *Areas Reserved for Domestic Investors*
The areas of investment listed in the Schedule attached to these Regulations shall be exclusively reserved for domestic investors.

፬· ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፭ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Effective Date*

These Regulations shall come into force as of the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 12th day of June, 1998.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## ሠንጠረዥ

## ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የሥራ መስኮች

፩· የሬዲዮና የቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት ፤
፪· የችርቻሮ ንግድና የድለላ ሥራ ፤
፫· የጅምላ ንግድ (ነዳጅና የነዳጅ ምርቶችን ማቅረብ እንዲሁም የውጭ ባለሀብቶች በአገር ውስጥ ያመረቱትን በጅምላ መሸጥን ሳይጨምር) ፤
፬· የገቢ ንግድ ፤
፭· ጥሬ ቡና ፣ የቅባት እህሎችን ፣ ጥራጥሬ ፣ ቆዳና ሌጦ እንዲሁም ኢንቨስተሩ ራሱ ካረባቸው ወይም ካደለባቸው በስተቀር በጐችን፣ ፍየሎችንና የቀንድ ከብቶችን በቁም ወደ ውጭ መላክ፤
፮· ደረጃ አንድ ከሚመደቡት በስተቀር የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጭነት ፤
፯· ቆዳና ሌጦ እስከ ክረስት ደረጃ ማልፋት ፤
፰· የባለኮከብ ደረጃዎችን የማይጨምሩ ሆቴሎች ፣ ሞቴሎች ፣ ፔንሲዮኖች ፣ ሻይ ቤቶች ፣ ቡና ቤቶችና መጠጥ ቤቶች ፣ የምሽት ክበቦች ፣ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ካላቸውና በተወሰነ አገር ምግብ አዘገጃጀት ከሚታወቁት በስተቀር ሌሎች ምግብ ቤቶች ፤
፱· የማስጐብኘት አገልግሎት ፣ የጉዞ ወኪልነት የኮሚሲዮን ወኪልነትና የቲኬት መሸጫዎች ፤
፲· መኪና የማከራየትና የታክሲ አገልግሎት ፤
፲፩· የመንገድ የንግድ ትራንስፖርት አገልግሎትና የሀገር ውስጥ ውሃ ላይ ትራንስፖርት አገልግሎት ፤
፲፪· ለሀገር ውስጥ ገበያ ብቻ የሚቀርቡ የዳቦና የኬክ ምርቶች ፤
፲፫· ወፍጮ ቤቶች ፤
፲፬· ፀጉር ማስተካከል ፣ የቁንጅና ሳሎን ፣ የአንጥረኝነት ሥራ በፋብሪካ ደረጃ የማይካሄድ የልብስ ስፌት ፤
፲፭· የሕንፃ እድሳትና የመኪና ጥገና አገልግሎት ፤
፲፮· የእንጨት መሰንጠቂያና የጣውላ ሥራዎች ፣ እንዲሁም ለሀገር ገበያ ብቻ የሚቀርቡ የእንጨት ሥራ ውጤቶችን ማምረት ፤
፲፯· የጉምሩክ አስተላላፊነት ሥራ ፤
፲፰· የሙዚየም ፣ የቲያትርና የሲኒማ ማሣየት አገልግሎት ፤
፲፱· የሕትመት ሥራ ፤
፳· ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ።

## *Schedule*

### *Areas of Investment Reserved for Domestic Investors*

1. Radio and television broadcasting services;
2. Retail trade and brokerage;
3. Wholesale trade (excluding supply of petroleum and its by-products as well as wholesale by foreign investors of their products, locally produced;
4. Import trade;
5. Export trade of raw coffee, oil seeds, pulses, hides and skins and live sheep, goats and cattle not raised or fattened on own farm;
6. Construction companies excluding grade 1 contractors;
7. Tanning of hides and skins up to crust level;
8. Hotels other than those star-designated, motels, pensions, tearooms, coffee shops, bars, night clubs and restaurants excluding international and specialized restaurants;
9. Tour operations, travel agency, commission agency and ticket offices;
10. Car hire and taxi-cabs transport;
11. Commercial road transport and inland-water transport services;
12. Bakery products and pastries exclusively for the domestic market;
13. Grinding mills;
14. Barber shops, Beauty salons, smith workshops and tailoring excluding garment factories;
15. Building maintenance services, repair and maintenance of vehicles;
16. Saw mills and manufacture of wood products exclusively for the domestic market;
17. Customs clearnace services;
18. Museums, theaters and cinema hall operations;
19. Printing industry;
20. Artisanal mining.